AMHARIC

ተ መ ሳ ሳ ይ  ሙ ያ  ባ ላ ቸ ው
እ ኩ ያ ዎ ቻ ች ን  አ ማ ካ ኝ ነ ት  የ ተ ደ ረ ገ
ግ ም ገ ማ ና  የ ማ ጠ ቃ ለ ያ  ሃ ሳ ብ

# የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች(ELL)



የሲያትል አብያተ ትምህርት የተለያዩ የትምህርትና የአሰራር ጉዳዮችን በሚመለከት ተመሳሳይ ሙያ ባላቸው እኩያዎቻችን peer reviews) አማካይነት ግምገማዎችን አካሂዷል። ይህ አገር አቀፍ በሆኑ ሙያተኞች የተደረገ ግምገማ ደግሞ በጥሩ ሁኔታ በመካሄድ ላይ ያለውንና ማሻሻል የሚገባንን ደግሞ እንድናውቅ ጠቁሞናል።

ከእነዚህ ገምጋሚዎች የተገኘው እያንዳንዱ ምክርና አስተያየት ለትምህርት ቤቶች አስተዳደር የስትራተጂክ ፕላን አሰራር መረጃን በመስጠትና በእያንዳንዱ ፕሮግራም ላይ ለውጥና ማሻሻያን በማድረግ በአጠቃላይ በፊታችን ያለውን ራእይ እንዲጐለብት ያደርገዋል። .

የሲያትል ከተማ ከተመሰረተች ጀምሮ የተለያዩ ህዝቦች ከሁሉም የአለም አካባቢ ሰብስባለች። በዚህ ምክንያት የሲያትል አብያተ ትምህርት ቤት የተለያየ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑና በርካታ የተለያየ ችሎታ ያላቸውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ በማስተማር አገልግሎት ሰጥታለች።

ለምሳሌ በ 2005-2006 የትምህርት አመት 23% የሚሆኑት ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ነበሩ።። ከአገሪቱ ጋር ሲወዳደር ደግሞ 9% ይሆናል። ከእነዚህ ውስጥ በግምት 25% ቀዳሚውን ቦታ የያዙት ስፓኒሽ፣ በመቀጠልም ቬትናሚዝ፣ካንቶኒዝ፣ታጋሎግና ሶማሊያ ይገኙበታል።

እነዚህን ተማሪዎችና ቤተሰቦቻቸውን ለማገልገል ደግሞ በሲያትል በ 56 አብያተ ትምህርት ቤቶች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም እንዲኖር፣ የሚመዘገቡበት ደግሞ የባይሊንጓል ቤተሰብ ማእከል፣ አንድ የሁለተኛ ደረጃ የባይሊንጓል መተዋወቂያ ማእከልና ሶስት የአንደኛ ደረጃ የባይሊንጓል የመተዋወቂያ ማእከል በመክፈት ለአሜሪካ አዲስ መጪ የሆኑትንና የተወሰነ የእንግሊዝኛ ችሎታ ያላቸውን አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

## ገምጋሚዎች

ይህ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን በሚመለከት የተደረገው ጥናት የተካሄደው በታላላቅ ከተማዎች የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ኮሚቴ (Council of the Great City Schools.) አማካይነት የተደረገ ነው።ይህ ኮሚቴ በ 1956 የተመሰረተና በ 66 ከተሞች በሚገኙ ታላላቅ የህዝብ ትምህርት ቤቶችን ህብረት ያቀፈ ነው። ይህ ኮሚቴ አባል የሆኑ ትምህርት ቤቶችን በተለያየ መልኩ ማለት አስተዳደርን ጥናትን በማካሄድ፣ ብኮሚኒኬሽን፣ በስርአተ ትምህርትና በአሰራር ሁኔታዎች ላይ እርዳታን የሚሰጥና ባለፉት በርካታ አመታት 150 የሚሆን የትምህርት፣የአስተዳደርና አሰራርን በሚመለከት ግምገማዎችን አድርጓል። የተደረገው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ግምገማ ፡ኮሚቴው የተለያዩ ተማሪዎችን ያቀፈ ከ ሌሎች ትላልቅ ከተሞች የሚገኙ የትምህርት ቤት አስተዳደሮችና የተለያዩ የስርአተ ትምህርት መሪዎች የሚገኙበት ኮሚቴን በማቆም የተደረገ ነው።

## የማጠቃለያ ሃሳብ

ግምገማውን ያካሄደው ኮሚቴ የሲያትል አብያተ ትምህርት መስተዳድር መሪዎች ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚሰጠውን አገልግሎት ለማሻሻልና ለማጠናከር ያሳዩትን ፍላጐት በማሞገስ ፣ ሲያትል አለም አቀፍ ማእከል እንደመሆኗ መጠን፡ ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር የሚሄድ የእንግሊዝኛ ቋንቋ አገልግሎትን ለመስጠት ከዚህ በፊት ያልታየ እድል እንዳላት ገልጸዋል። ነገር ግን በተለያዩ ረገዶች 43% የሚሆኑት የባይሊንጓል አገልግሎት አለማግኘታቸውንና ፣ በትምህርት ቤቶች የሚሰጠው ትምህርት ደግሞ ተመጣጣኝና እኩል አለመሆኑን፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች እድገት መሻሻል በቅርቡ እየቀነሰ መምጣቱ እንዳሳሰባቸው ገልጸዋል።

ግምገማውን ያደረገው ቡድን ስራውን ካጠናቀቀ በኋላ በ 12 ልዩ ልዩ መስኮች መስተካከል ያለባቸውን ጠቁሟል። ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ ፕሮግራሞችን መንደፍ፣ ስርአተ ትምህርትና(ካሪኩለም)፣ እንዲሁም ሃላፊነትን ማክበር(ኮምፕላያንስ) የመሳሰሉት ይገኙበታል። ይህ እንዲስተካከል የቀረበው ሓሳብ በእያንዳንዱ ፕሮግራም ላይ አስተያየትን ሰጥቷል። ቡድኑ ሲያትል የምትሰጠውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት አገልግሎት በሚመለከት ቀጥሎ የተጠቀሰውን አስተያየት በመስጠት እንዲታሰብበትና ብሌላ መልኩ እንዲቀየር አሳስቧል፤

- የእንግሊዝኛ ቋንቋ እንደሁለተኛ ቋንቋ በመጠቀም ከክፍል ውስጥ አውጥቶ የሚሰጥ ድጋፍ(ፑልአውት) መቀነስና በምትኩ ግን ሼልተርድ ኢንግሊሽ ፕላስ( ኮንቴንት ኢኤስ ኤል) የተሰኘውን ሞዴል ለመጠቀም የሚያስችል በዲስትሪክቱ ካሪኩለም መነደፍ እንዳለበት፤ የተማሪዎችን ትምህርት እድገት ሊያጐለብት የሚችል የሁለት ቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም እንዲሰጥ ሃሳብ ሰጥቷል።
- ፕሮግራሞቹ በይበልጥ ለተማሪዎችና ለቤተሰቦቻቸው በቅርብ አካባቢ እንዲሆኑና የበለጠ የመሸጋገሪያ ዘዴን ለመፍጠርና የተማሪዎችን የመመረቅ እድል የተመቸ እንዲሆን ለማድረግ የባይሊንጓል የመተዋወቂያ ማእከሎች(ቢኦሲ) አወቃቀራቸውን መለወጥ ፤
- የሲያትል ከተማ የአለም አቀፍ መግቢያ በር መሆኗን ለማንጸባረቅ በሁሉም ትምህርት ቤቶች ለሁሉም ተማሪዎች እድል የሚሰጥ የሁለት ቋንቋ ፕሮግራሞችን የያዘ ትምህርት እንዲዘጋጅ ማድረግ የሚሉት ይገኙበታል።

## የአጠናኑ ዘዴ

ግምገማውን ያደረገው ኮሚቴ በ 2008 መጀመሪያ አካባቢ ሁለት ጊዜ ወደ ሲያትል በመምጣት ግምገማውን አካሄደ። በ 14 ትምህርት ቤቶች የሚገኙ 100 ክፍሎችን በምታዘብ፣ ሰነዶችንና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ስርአተ ትምህርት ማቴሪያሎችን በመመርመር፣ ከአስተማሪዎች፣ ከረዳት አስተማሪዎች ጋር በመገናኘት፤ ከትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎችና ከሲያት አብያተ ትምህርት አስተዳደር መሪዎች ጋር ተገናኝተዋል። የመጨረሻው ሪፖርት ደግሞ በ ነሃሴ(ኦገስት) ወር 2008 እንዲቀርብ ተደርጓል።

## የግምገማው ውጤትና መሻሻል የሚያስፈልጋቸውን በሚመለከት የተሰጠ አስተያየት

ግምገማውን ያካሄደው ኮሚቴ 12 የተለያዩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ፕሮግራሞችን በማጥናት በእያንዳንዱ ፕሮግራም ላይ መሻሻል የሚገባውን ጠቁሟል ፤

### አመራርና ስትራተጂያዊ የሆነ አቅጣጫ፤

ኮሚቴው የሲያትልን አመራርና የቦርድ ፖሊሲ ቢያደንቅም ነገር ግን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ፕሮግራም በሚመለከት ሲያትል ግልጽ የሆነ ራእይ ወይ ስትራተጂ እንደሌላትና፣ የሚደረገውን የእድገት መሻሻል ለቦርዱ ሪፖርት ለማድረግ ግልጽ የሆነ አሰራር አለመኖሩ ያሳሰባቸው መሆኑን ገልጸዋል። ኮሚቴው የሲያትል ትምህርት ቤቶች መሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ፕሮግራሞች ግልጽ የሆነ አቅጣጫ እንዲኖራቸውና ይህም አቅጣጫ ከስትራተጂክ ፕላኑ ተግባራዊነት ጋር እንዲዛመድ ገልጿል።

# የግምገማው ውጤትና መሻሻል ስለሚገባቸው ጉዳዮች የተሰጠ ኣስተያየት(የሚቀጥል)

**ኣላማና ተጠያቂነት፤** ኮሚቴው በሲያትል በመማር በኩል ያለው ክፍተት(አችቨመንት ጋፕ) ግብ በሲያትል ታሪክ ውስጥ ዘርንና የገቢ ሁኔታን በግምት ውስጥ በማስገባ እንጂ በቋንቋ መሰናክሎች አለመሆኑን ገልጿል። የኮሚቴው አባላት የሲያት አብያተ ትምህርት ቤቶች በቋንቋ ቡድን በኩል ግልጽ የሆነ ትምህርታዊ ግቦችን እንዲነድፉና በየጊዜው ደግሞ ትምህርት ቤቶችን መገምገም እንዳለባቸው ጠቁሟል። ይህ አስተያየት በስትራተጂክ ፕላኑ ላይ የክንውን አስተዳደርንና(ማናጅመንት) ከሚመለከተው ጋር የተዛመደ ነው።

**ፕሮግራም መንደፍና የአተገባበር አሰራር፤** ኮሚቴው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች መካከል ያለው እድገት ዝቅተኛነት ያሳሰበው መሆኑን በመግለጽ አሁን በሲያትል የሚጠቀሙበት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ ሞዴል በትምህርታዊ ድል ላይ አትኩሮ እንደሌለው ገልጿል። ኮሚቴው በሲያትል ከተማ ግልጽ የሆነ ግብ ያለውና ልዩነቶችን በግምት ውስጥ የሚያስገባ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም እንዲያዘጋጅ አሳስቧል። በተለይ ደግሞ የኮሚቴው አባላት የሲያትል ትምህርት ቤቶች አሁን የሚጠቀሙበት ከክፍል አውጥቶ ድጋፍ መስጠት አሰራር እንዲቀንስና በምትኩ ሼልተርድ ኢንግሊሽ ፕላስ(ኮንቴንት ኢኤስኤል) የሚባል ሞዴል እንዲተካና በአንዳንድ የከተማይቱ ክልሎች የሁለት ቋንቋ የትምህርት ፕሮግራም ያላቸው ትምህርት ቤቶች እንዲኖሩ አሳስቧል።

**ስርዓተ ትምህርትና የትምህርት አሰጣጥ፡** ኮሚቴው የሲያትል ትምህርት ቤቶች መሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ስርዓተ ትምህርትን(ካሪኩለም) በሚመለከት ያሳዩትን ፍላጐት በማድነቅ ፡ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት የሚሰራበት የስርአተ ትምህርት ማቴሪያሎች ጊዜያዊና ከስቴት መምዘኛዎች ጋር በይበልጥ እንዲዛመድ አለመደረጉን ገልጿል። ኮሚቴው የሲያትል አብያተ ትምህርት የተቀነባበረና በመላው ዲስትሪክ የሚሰራበት ካሪኩለም እንዲያዘጋጅና የመማሪያ መጽሃፎችን ደግሞ አስተማሪዎችና ረዳት አስተማሪዎች(አይኤ) በምን መልኩ ተጨማሪ እርዳታ መስጠት እንደሚችሉ መመሪያ ማግኘት እንዳለባቸው ጠቅሷል። ኮሚቴው የሲያትል አብያተ ትምህርት ተማሪዎች በስቴቱ የሚሰጡ የመመዘኛ ፈተናዎችን ለማለፍ ዝግጁ እንዲሆኑ፡ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች በቀዳሚነት የሂሳብና የንባብን ትምህርት በሚመለከት ትኩረት እንዲደረግ አሳስቧል።

**ጭብጥና(ዳታ) ግምገማ:** ኮሚቴው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የሚመለከቱት ዳታዎች ከሌሎች ተማሪዎ የተገለለና፡ ተማሪዎች ወደ መደበኛ ፕሮግራም በሚሸጋገሩበት ወቅት ያሳዩትን እድገት ለመቆጣጠር አስቸጋሪ እንደሚያደርገው ገልጸዋል። ኮሚቴው የሲያትል አብያተ ትምህርት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ዳታ በሁሉም ትምህርት ቤት ሊቀመጥበት የሚችል አሰራር እንዲኖርና የተማሪዎችን የፈተና ነጥቦች በመከታተልና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ፕሮግራሞች ላይ በሚያጠፉት ጊዜ ላይ ማተኮር እንዳለባቸው አሳስበዋል።
.

**የተማሪዎች አመዳደብ፤** ኮሚቴው የሲያትል የተማሪዎች አመዳደብ ፕላን አብዛኛውን ጊዜ ረጂም ጉዞ የሚያስኬድና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችም ሁኔታ ውሱን ማረጋገጫ እንዳለው ገልጿል። እንዲሁም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቤተሰቦች በሁለት የተለያዩ ቦታዎች( የባይሊንጓል ቤተሰብ ማእከልን ጨምሮ) ማመልከቻዎችን እንዲሞሉ አሳስቧል። ኮሚቴው እንዲሁም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች አገልግሎቶች በቀላሉ እንዲሰጥ በመላው ዲስትሪክት መሰራጨት እንዳለበት አሳስቧል።

**ሰራተኞችና ስልጠና፤** ኮሚቴው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ሰራተኞች ቁጥር ከሌሎች ዲስትሪክቶች ጋር በማነጻጸር ለመጨመር ግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለበት፣ ተጨማሪ ስልጠናና አቅጣጫ ለትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች፣ ለአስተማሪዎችና ለረዳት አስተማሪዎች መሰጠት እንዳለበት አሳስቧል።

**ረዳት አስተማሪዎች(አይ.ኤ)** ኮሚቴው ረዳት አስተማሪዎች ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ፕሮግራም ጠቃሚ መሆናቸውን በመግለጽ፡ የረዳት አስተማሪዎች የስራ ድርሻ በማስተማርና በማስተርጎም ያለው ሃላፊነት በግልጽ መለያየት እንዳለበት ጠቅሰዋል።

**የባይሊንጓል መተዋወቂያ ማእከሎች፤** ኮሚቴው አሁን ያለው የባይሊንጓል መተዋወቂያ ማእከሎች ለረጅም ሰአታት እንዲጓዙ የሚያደርጋቸውን ከማእከሉ ወደ መደበኛ ትምህርት ቤቶች እንዲሸጋገሩ የሚሰጠው ድጋፍ ውሱን መሆኑን በመጥቀስ፡ ይህ መዋቅር በአዲስ መልክ እንዲዋቀር በማሳሰብ የአንደኛ ደረጃ መተዋወቂያ ማእከሎች በአካባቢ ትምህርት ቤቶች እንዲሆኑ፤ ከ 6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ያሉት ደግሞ በመለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሆኑ፤ የሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አለም አቀፍ ይዘት ያለው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሆኖ ተማሪዎች ነጥብ የሚያገኙበትና ሊመረቁበት የሚችሉበት እንዲሆን አሳስበዋል። እንዲሁም የሲያትል ትምህርት ቤቶች አስተዳደር ከመተዋወቂያ ማእከሎች ወደ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ለመሸጋገር የሚያስችል ግልጽ የሆነ አሰራር እንዲኖረውና ለባይሊንጓል ተማሪዎች ትምህርታቸው ለማጐልበት ትኩረት መስጠት እንዳለበት ገልጸዋል።

# የግምገማው ውጤትና መሻሻል ስለሚገባቸው ጉዳዮች አስተያየት(የሚቀጥል)

**ወላጆችና ኮሚኒቲ፡** ኮሚቴው የሲያትል ትምህርት ቤቶች ቤተሰቦችን ለመድረስ በማድረግ ላይ ያለውን ጥረት አድንቋል። ነገር ግን ብዙ ቤተሰቦች ስለሚሰጡት አገልግሎቶች በጣም አነስተኛ መረዳት እንዳላቸው በመግለጽ የሲያትል አብያተ ትምህርት አስተዳደር በማድረግ ላይ ያለውን ጥረት በመቀጠል የተለያዩ ኮሚኒቲዎችን እንዲደርስ አሳስቧል።

**ባጀትና የገንዘብ ምንጪ፤** ኮሚቴው የሲያትል አብያተ ትምህርት የሚያደርገውን ጥረት በእጥፍ በመቀጠል ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ፕሮግራሞች ተብሎ የሚፈቀዱ የአካባቢ፣ የስቴትና የፌደራል ገንዘብን እንዲጠቀሙ አሳስቧል።

**ግዴታን ማክበር (Compliance)** ኮሚቴው ከሰጣቸው አጠቃላይ አስተያየቶች ጋር የሚዛመድ የሲያትል ትምህርት ቤቶች በጠንካራና በበለጠ ትምህርት ላይ የሚያተኩርና የፌደራልንና የስቴትን መመዘኛዎችን ሙሉ በሙሉ ለማክበር የሚጠቅም አዲስ የሰራተኞች የመረጃ መጽሃፍ(ሃንድ ቡክ) እንዲዘጋጅ አሳስቧል።



## NEXT STEPS

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ፕሮግራሞች ግምገማ የተደረገበት ምክንያት የሲያትል ትምህርት ቤቶች የስትራተጂን ፕላን ለመቀየስ ባደረገው አሰራር ላይ አንዱ አካል በመሆኑ ነው። “ ለሁሉም እጅግ ጥሩ፤ የተሰኘ የስትራተጂክ ፕላን የሁሉንም ተማሪዎች የትምህርት እድገታቸውን ከፍ ለማድረግ እንዲረዳ፣ አሁን ያለንበትን ሁኔታ እንድናውቅና ማሻሻል የሚገባንን እንደአስፈላጊነቱ አውቀን እርምጃ እንድንወስድ የሚረዳ ነው። የስትራተጂክ ፕላኑ በትምህርት ቤቶች ቦርድ በሰኔ ወር 2008 የጸደቀና በፊታችን ባሉት አመታት በተግባር ላይ የሚውል ነው።

*Photographs © 2008 Susie Fitzhugh.*